# የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ

# የ2013 በጀት ዓመት ዕቅድ

ሰኔ 2012 ዓ/ም

አዲስ አበባ

ማውጫ

1. መግቢያ ........ 2
ክፍል አንድ፡- የእቅዱ መነሻ ሁኔታዎች፣ ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች፣ ........ 3
1.1. የእቅዱ መነሻ ሁኔታዎች ........ 3
1.1.1. የከተማ ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂዎች ........ 3
1.1.2. የትብብር መድረኩ ስትራቴጂክ ዕቅድ ........ 3
1.1.3. የ2012 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ........ 4
1.2. ትኩረት የሚሹ ጉዳዩች ........ 4
1.3. ራዕይ እና ተልዕኮ ........ 5
1.3.1. ራዕይ ........ 5
1.3.2. ተልዕኮ ........ 5
ክፍል ሁለት፡- የበጀት ዓመቱ ዕቅድ ........ 5
2.1.1. የትብብር መድረኩን ተቋማዊ አቅም ለማጠናከር የሚረዱ ግቦችና ዝርዝር ተግባራት ........ 6
2.1.2. የትብብር መድረኩን ዓላማና ተልዕኮ ለማሳካት የሚያስችሉ ግቦችና ተግባራት ........ 11
2.4. እቅዱን በመተግበር ሂደት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ታሳቢ ስጋቶችና የመፍትሄ እርምጃዎች ........ 18
2.4.1. ታሳቢ ስጋቶች ........ 18
2.4.2. ታሳቢ የመፍትሄ እርምጃዎች ........ 18
ክፍል ሦስት፡- የክትትል፣ ግምገማና ግብረ መልስ ሥርዓት ........ 19
ማጠቃለያ ........ 19

1. መግቢያ

የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት በከተሞች የሚታየውን ያልተመጣጠነ ዕድገት፣ ድህነትና ስራ አጥነት ለመቅረፍ ከተሞች የዕርስ በርስ ግኑኝነታቸውን በማጠናከር፣ ከሌሎች መልካም ተሞክሮ ካላቸው የአገር ውስጥም ሆነ ከውጭ አገር ከተሞች የልምድ ልውውጥ በማድረግ ጠቃሚ አማራጮችንና ልምዶችን በመውሰድና በመቀመር በአባል ከተሞች የማስፋፋት ስራ እንዲሁም በፖሊሲና በከተማ አመራር ጉዳዮች ላይ የራሱን ድርሻ ለመወጣት እንደዋነኛ አጀንዳ ይዞ በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡ እነዚህን የተቀመጡ አላማዎችን ለማሳካት የከተሞችን ፍላጎት በማካተት፣ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴና የጠቅላላ ጉባኤውን አቅጣጫና የሴክተሩን ስትራተጂክ ጉዳዮችና ዕቅዶች እንዲሁም የ2012 የትብብር መድረኩን አመታዊ ዕቅድ አፈጻጸም እና ከ2002-2009 የተከናወኑ ስራዎች እንዲሁም የ3 አመቱ ስትራተጂክ ዕቅድን (2010-2012) ግምት ያስገባ የ2013 ዕቅድ ተዘጋጅቷል፡፡

በትብብር መድረኩ ስትራቴጂክ ዕቅድ ሰነድ ላይ በግልጽ እንደተቀመጠው የአምስት አመቱ ዋና ዋና ስራዎች በየአመቱ ተከፋፍለው እንዲሰሩ የድርጊት መርሀ ግብር ተዘጋጅቷል፡፡ በዚህም መሰረት በ2012 በጀት ዓመት ከተሞች ዘላቂ ልማት የሰፈነባቸው፣ ለነዋሪዎቻቸው ምቹ እንዲሆኑ እና መልካም አስተዳደር የሰፈነባቸው እንዲሆኑ ለማድረግ የተለያዩ ስራዎችን ሲያከናውን ቆይቷል፡፡ የበጀት ዓመቱን እቅድ አፈጻጸም መነሻ በማድረግም በአፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችንና ድክመቶችን ገምግሟል፡፡

በ2013 በጀት ዓመትም በቀጣይ የአፈጻጸም ስልቶችና የትኩረት አቅጣጫዎች ቅኝት አንጻር አሁን ያሉ ችግሮችን በመፍታትና መልካም ጅምሮችን አጠናክሮ በማስቀጠል፤ የአባል ከተሞችን አመራርና ፈጻሚዎችን የዕውቀትና የክህሎት ክፍተታቸውን በመሙላት፤ ብቃታቸውን በማሳደግና ከተሞች ለነዋሪዎቻቸው ምቹ የልማትና የመልካም አስተዳደር ማዕከላት ለማድረግ የሚስችሉ ሥራዎችን ለማከናወን ታቅዷል፡፡

ይህ ዕቅድ በትብብር መድረኩ ስር የተዋቀሩትን የስራ ክፍሎች ማለትም የሪሶርስ ሞቢላይዜሽንና እውቀት ስራ ዳይሬክቶሬት፣ የኮሚኒኬሽንና ኔትወርኪንግ ዳይሬክቶሬት እና የአስተዳደርና ፋይናንስ ዳይሬክቶሬትን ዝርዝር ዕቅድ በማካተት በሶስት ክፍሎች ተደራጅቶ

ቀርቧል፡፡ የመጀመሪያው ክፍል የዕቅዱን መነሻ ሁኔታዎች የሚተነትን ሲሆን በክፍል ሁለት የትብብር መድረኩን የበጀት ዓመቱ ስራዎች የተቀመጡበት ነው፡፡ ክፍል ሶስት የክትትል፣ ግምገማና ግብረ-መልስ ሥርዓት የያዘ ክፍል ነው፡፡

**ክፍል አንድ፡- የእቅዱ መነሻ ሁኔታዎች፣ ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች፣**

## 1.1. የእቅዱ መነሻ ሁኔታዎች

የዕቅዱ መነሻ የሆኑት በዋናነት የከተማ ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂዎች፣ የትብብር መድረኩ ስትራቴጂክ ዕቅድ እና የ2012 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ናቸው፡፡

### 1.1.1. የከተማ ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂዎች

የከተማ ልማት ፖሊሲን እና ፖሊሲውን መነሻ በማድረግ የወጡ ስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞች፣ የከተማ ምግብ ዋስትናና ልማታዊ ሴፍቲኔት (የሥራ ዕድል ፈጠራ ማሳፋት) ፕሮግራም፣ የከተሞች ልማታዊ መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ ፕሮግራም፣ የከተማ ፕላን ዝግጅትና አፈጻጸም ፕሮግራም፣ የመሬት ልማትና አስተዳደር ማሻሻል ፕሮግራም፣ የከተማ ካርታ ማምረት፣ የቅየሳና የመሬት መጠቀም መብት ምዝገባ ፕሮግራም፣ የከተማ ቤት ልማትና አስተዳደር ንዑስ ፕሮግራም፣ የተቀናጀ የከተሞች መሰረተ-ልማት አቅርቦት ፕሮግራም፣ የከተሞች ፋይናንስ ልማትና አመራር ፕሮግራም፣ የከተሞች የአረንጓዴ ልማትና ጽዳት ማሻሻያ ፕሮግራም፣ ተደራሽነትንና የህዝቡን ደህንነት የሚያረጋግጥ የከተማ ልማት ኘሮግራም ለዕቅዳችን መነሻ ተደርገው ተወስደዋል፡፡

### 1.1.2. የትብብር መድረኩ ስትራቴጂክ ዕቅድ

ትብብር መድረኩ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴና የጠቅላላ ጉባኤውን አቅጣጫና የሴክተሩን ስትራተጂክ ጉዳዮች ታሳቢ በማድረግ ስትራተጂክ ዕቅድ አዘጋጅቷል፡፡ የ2013 በጀት ዓመት ዕቅድ ለማዘጋጀት እንደመነሻ ተወስዷል፡፡

### 1.1.3. የ2012 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም

በ2012 በጀት ዓመት ስምንት ግቦች የተጣሉ ሲሆን ከግቦቹም መካከል አብዛኞቹ ሊባል በሚችል ደረጃ በመልካም ሁኔታ የተከናወኑ ሲሆን የተቀሩቱ በሂደት ላይ ይገኛሉ፡፡ የ2012 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸምና የተገኙ ውጤቶች የዕቅዱ መነሻ ናቸው፡፡

## 1.2. ትኩረት የሚሹ ጉዳዩች

በ2013 በጀት ዓመት የትብብር መድረኩ የትኩረት አቅጣጫዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

- የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ ስትራቴጂክ እቅድ ማዘጋጀት፣
- የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም የፋይዳ ዳሰሳ ጥናት ወደ ትግበራ እንዲሸጋገር ማድረግ፣
- የከተሞች አመራሮችና ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት፣
- በከተሞች እህትማማችነት ጉድኝት ለመመስረትና ለማጠናከር የሚያስችል የአሰራር ማንዋልና ደረጃውን የጠበቀ የከተሞች ፕሮፋይል ማዘገጀት፣
- የትብብር መድረኩ ሰራተኞችን አቅም ለማጎልበት በስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ መሰረት በተመረጡ የስልጠና ዓይነቶች ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፣
- በየ2 አመቱ ለሚካሄደው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም የተሳታፊ ከተሞች ምዝገባ እና የኮሚኒኬሽን ስራ በትብብር መድረኩ ሊከናወን የሚገባ ስራ በመሆኑ ከመንግስት ጋር በመወያየት ሥራውን ለመስራት ሃላፊነት መውሰዱ ትኩረት የሚያሻው ጉዳይ ነው፣
- አመታዊ የአባልነት መዋጮ ውዝፍ ዕዳ ያለባቸውን ከተሞች በማግባባት ክፍያቸውን እንዲፈጽሙ ማድረግ ትኩረት የሚያሻው ጉዳይ ነው፣
- የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ የአባል ከተሞች ቁጥር ከፍ እንዲል ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው፣
- ወሳኝ በሆኑ የትብብር መድረኩ ክፍት የስራ መደቦች ላይ አቅምን ባገናዘበ መልኩ መሞላት ያስፈልጋል፣
- አመታዊ የአባልነት መዋጮ በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ መሰብሰብ ቢቻል የተሻለ አፈጻጸም ለማምጣት ስለሚያስችል በአባል ከተሞች በኩል ትኩረት የሚፈልግ ጉዳይ ነው፣
- ትብብር መድረኩ ለእለት ተዕለት ስራ ማስኬጃ ምቹ ቢሮ መፍጠር በዘላቂነት ሊታሰብበት የሚገባ ነው፡፡

### 1.3. ራዕይ እና ተልዕኮ

#### 1.3.1. ራዕይ

"ለኑሮምቹ የሆኑ፣ ዘላቂ ልማት የተረጋገጠባቸው፣ መካከለኛ ገቢ ያላቸው፣ ምርታማና በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆኑ ከተሞች በ2030 ተፈጥረው ማየት"፡፡

#### 1.3.2. ተልዕኮ

- ከተሞች ልምዳቸውን የሚለዋወጡበት መድረክ ሆኖ ማገልገል፤
- ከተሞችን በሚመለከቱ የፖሊሲ ውይይት የሚደረጉባቸው መድረኮችን ማመቻቸት፤
- ምርጥ ተሞክሮዎችን መለየት፤ መቀመር፤ ለአባል ከተሞች ማሰራጨት፤
- የእህት ከተሞች ምስረታ ማመቻቸት፤ ማበረታታት፤
- ለፋይናንስና የሰው ሃይል አቅም ግንባታ እና ለከተሞች ትስስር መስራት፤
- መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር የትብብር ግንኙነት በመፍጠር ለአባል ከተሞች ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት እና፤
- አባል ከተሞች አለምዓቀፍ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ መስራት፡፡

## ክፍል ሁለት፡- የበጀት ዓመቱ ዕቅድ

### ጥቅል ዓላማ

የከተሞች አመራርና ፈጻሚዎችን የዕውቀትና የክህሎት ክፍተታቸውን በመሙላትና ብቃታቸውን በማሳደግ ከተሞች ለነዋሪዎቻቸው ምቹ የልማትና የመልካም አስተዳደር ማዕከላት ማድረግ ነው፡፡

### ጥቅል ግብ

ለትብብር መድረኩ አባል ከተሞች አመራርና ባለሙያዎች በከተማ ልማት አጀንዳዎች ዙሪያ የአቅም ግንባታ ስልጠና በመስጠት፣ የልምድ ልውውጥ አውደጥናቶችን በማካሄድ ከተሞች የዕርስ በርስ ግንኙነታቸውን እንዲያጠናክሩ በማድረግ ከተሞች በአህጉር ብሎም በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

### 2.1.1. የትብብር መድረኩን ተቋማዊ አቅም ለማጠናከር የሚረዱ ግቦችና ዝርዝር ተግባራት

**ግብ 1፡- የትብብር መድረኩን የሩብ ዓመት፣ የግማሽ ዓመት እና ዓመታዊ የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ጥራቱንና ጊዜውን ጠብቆ እንዲዘጋጅ በማድረግ መገምገምና አፈጻጸሙ እንዲሻሻል ይደረጋል፡፡**

ተግባር 1፡- የዳይሬክቶሬቶችን ዕቅድ በወቅቱ ማቅረብና መገምገም፣

ተግባር 2፡- የዳይሬክቶሬቶቹን የግቦች አፈጻጸም ሪፖርት መለኪያውና ዒላማው እርስ በርስ የተናበበ ማድረግ፣

ተግባር 3፡- በትብብር መድረኩ ስራ አስፈጻሚ ቦርድ የሚሰጡትን አቅጣጫዎች፣ ውሳኔዎች እና አስተያየቶች እንዲሁም ግብረመልሶችን ተቀብሎ ተግባራዊ ማድረግ፣

**ግብ 2 ፡- የትብብር መድረኩን የሂሳብ አያያዝ ስርዓት የማዘመን ስራ ይከናወናል፡፡**

ተግባር 1፡-ዝክረ ተግባር ማዘጋጀት፤

ተግባር 2፡ ግልጽ ጨረታ ማውጣት፣

ተግባር 3፡ የተጫራቾችን ሰነድ መገምገምና መለየት፣

ተግባር 4፡ ከአሸናፊ ድርጅት ጋር ውል መግባት፡

ተግባር 5፡- የትብብር መድረኩን የፋይናንስ ስርዓት ለማዘመን የIPSAS ሶፊትዌር ከነአሰልጣኙ በመግዛት ለማዘመን የተጀመረውን ስራ ማስጨረስ፤

ተግባር 6፡- የትብብር መድረኩን የበጀት ዓመቱን ሂሳብ መዝጋት፤

ተግባር 7፡- የድርጅቱን አመታዊ የፋይናንስ ሪፖርት በIPSAS ሶፊትዌር መሰረት ማዘጋጀት፤

ተግባር 8፡- የትብብር መድረኩን የበጀት ዓመቱን ገቢ እና ወጪ የኦዲት ሪፖርት በማስደረግ ለቦርድና ለጠቅላላ ጉባኤ በማቅረብ ማጸደቅ፤

ተግባር 9፡- የፀደቀውን የፋይናንስና ኦዲት ሪፖርት ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ኤጀንሲ ከመስከረም 30 ቀን በፊት ማስገባት፤

**ግብ 3፡- በትብብር መድረኩ የሚሰሩ ሥራዎችን አባል ከተሞች እንዲያውቋቸው በዓመት 4 ጊዜ ተደራሽ ይደረጋል፡፡**

ተግባር 1፡- በትብብር መድረኩ የሚዘጋጁ ስልጠናዎች፣ ዎርክሾፖች፣ የፓናል ውይይቶችና የምክክር መድረኮች የዘገባ ዜና ማቅረብ፤

ተግባር 2፡- በኮሚኒኬሽንና ኔትወርኪንግ ዘርፍ በኩል የሚያስፈልጉ መረጃዎችን በተደራጀ መልኩ ማጠናቀር፤

ተግባር 3፡- የትብብር መድረኩ የውስጥ እና የውጭ ተገልጋይ ተደራሽ እንዲደረግ የሚጠበቅ መረጃ በትብብር መድረኩ ዌብ ፖርታል፣ ፌስቡክ፣ ቴሌግራም ላይ እንዲጫን በማድረግ መረጃውን ተደራሽ ማድረግ፡፡

**ግብ 4፡- የትብብር መድረኩን ለአምስት ዓመታት (2013 — 2017 ዓ.ም) የሚያገለግል የስትራቴጂክ እቅድ ይዘጋጃል፡፡**

ተግባር 1፡- ዝክረ ተግባር ማዘጋጀት፤

ተግባር 2፡- የስራ ቡድን ("working group") ማቋቋም፤

ተግባር 3፡- መረጃ መሰብሰቢያ ቼክ ሊስት ማዘጋጀት፤

ተግባር 4፡- ከተመረጡ ከተሞች ባለሙያዎችን ማሰባሰብና ለእቅድ ዝግጅቱ ምቹ ሁኔታ ማመቻቸት፤

ተግባር 5፡- መረጃዎችን መተንተንና ረቂቅ ሰነድ ማዘጋጀት፤

ተግባር 6፡- በረቂቅ የስትራቴጂክ ጥናት ሰነዱ ላይ ግብዓት ማሰባሰብና ማዳበር፤

ተግባር 7፡- ረቂቅ እቅዱን የመጨረሻ ቅርፅ በማስያዝ ለስራ አስፈጻሚ ቦርድ በማቅረብ ማጸደቅ፤

**ግብ 5፡- በከተማ ልማት አጀንዳዎች ዙሪያ በለጋሽ ድርጅቶች በሚወጡ ማስታወቂያዎች መሰረት አራት የሃብት ማፈላለጊያ ኮንሴፕት ኖቶች እና ፕሮፖዛሎች ይዘጋጃሉ፡፡**

ተግባር 1፡ ማስታወቂያ መከታተል፤

ተግባር 2፡ ማስታወቂያ ያወጣውን ዶነር አስፈላጊ ሰነዶች ማንበብና መረዳት፤

ተግባር 3፡ በፎርማቶቹ መሰረት ኮንሴፕት ኖት ማዘጋጀት፤

ተግባር 4፡ ለአስተያየት ዝግጁ ማድረግ፣ አስተያየቶችን ማሰባሰብ፤

ተግባር 5፡ በተሰጡ አስተያየቶች መሰረት ሰነዱን ማዳበር፤

ተግባር 6፡ ለውድድር ማመልከት፤

ተግባር 7፡ የውድድር ሂደቱንና ውጤቱን መከታተል፤

**ግብ 6፡- የድርጅቱ ያልተሞሉ ክፍት የሥራ መደቦች ሲያስፈልግ ማሟላት**

ተግባር 1፡- ለድርጅቱ አስፈላጊ የሆኑ ክፍት የሆኑ የሥራ መደቦች መለየት፤

ተግባር 2፡- በድርጅቱ ህገ ደንብ መሰረት የውስጥ ወይም የውጭ ማስታወቂያ ማዘጋጀት እና ማውጣት፤

ተግባር 3፡- በድርጅቱ ህገ ደንብ መሰረት የአመልካቾች ሾርት ሊስት ማዘጋጀት፤

ተግባር 4፡- ሾርት ለሆኑት አመልካቾች የጽሁፍ እና የቃል ፈተናዎች ማዘጋጀት፤

ተግባር 5፡- አሸናፊ የሆነውን ሠራተኛ ደብዳቤ እና የሥራ ዝርዝር በመስጠት ቅጥሩን መፈፀም፤

ተግባር 6፡- ተቀጣሪውን የድርጅቱን ቅጥር ቅጽ ማስሞላት፤

ተግባር 7፡- ለአዲሱ ሠራተኛ ድርጅቱን የሚያውቅበትን ኢንዳክሽን እና ኦሬንቴሽን በማዘጋጀት ማሳወቅ፤

ተግባር 8፡- የሙከራ ጊዜውን ለሚጨርሱ ሠራተኞች ግምገማ ማካሄድ፣

ተግባር 9፡- ግምገማውን በተገቢው ውጤት ለሚያጠናቅቁ ሠራተኞች የቋሚ ደብዳቤ መስጠትና ስራ ማስጀመር፤

**ግብ 7፡- የድርጅቱ የተለያዩ መገልገያ ዕቃዎች ማሟላት**

ተግባር 1፡- የድርጅቱን እቅድ ለማስፈጸም የሚያገለግሉ የተለያዩ ቋሚ እቃዎች የመለየት ስራ መስራት፤

ተግባር 2፡- የቋሚ እቃዎች የፍላጎት መግለጫ በማዘጋጀት የግዢ ሰነድ ማዘጋጀት፤

ተግባር 3፡- የግዢውን ሰነድ ለአቅራቢ ድርጅቶች በመስጠት ፕሮፎርማ መሰብሰብ፤

ተግባር 4፡- በድርጅቱ ህገ ደንብ መሰረት ፕሮፎርማውን በማወዳደር ለአሸናፊው ድርጅት እውቅና መስጠት፤

ተግባር 5፡- ከአሸናፊው ድርጅት ትክክለኛው እቃ እንደሆነ በማረጋገጥ ግዢውን መፈጸም፤

**ግብ 8፡- የትብብር መድረኩ የጠቅላላ ጉባኤ እና መደበኛ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ስብሰባ ማካሄድ**

ተግባር 1፡- በደብዳቤና በስልክ አባል ከተሞች ጥሪ ማስተላለፍና ክትትል ማድረግ፤

ተግባር 2፡- ለስብሰባው የሚያስፈልጉ የሆቴል አገልግሎት ግዢ በድርጅቱ ህገ ደንብ መሰረት ፕሮፎርማ በመሰብሰብ ለሚያሸንፈው ድርጅት እውቅና በመስጠት ግዥ መፈፀም፤

ተግባር 3፡- ለስብሰባ ለተሳታፊዎች የውሎ አበል፣ የትራንስፖርት እና የሆቴል አገልግሎት ክፍያ መፈጸም፤

**ግብ 9፡- የትብብር መድረኩ ሰራተኞችን አቅም ለማጎልበት በስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ መሰረት በተመረጡ የስልጠና ዓይነቶች በዓመት አንድ የአቅም ግንባታ ስልጠና እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡**

ተግባር 1፡- ለድርጅቱ ሠራተኞች አስፈላጊውን የሥልጠና ለመስጠት ፍላጎታቸውን ለመለየት የሚያስችል መጠይቅ ማዘጋጀት፤

ተግባር 2፡- በመጠይቁ መሰረት መስፈርት በማዘጋጀት በአገር ውስጥ የስልጠና ተቋም መምረጥ፤

ተግባር 3፡- ሰልጣኞችን መለየት፤

ተግባር 4፡- በሚወጣው የስልጠና ፕሮግራም መሰረት ስልጠናው እንዲካሄድ ማድረግ፤

ተግባር 5፡- ሰልጣኞች ሪፖርት እንዲያቀርቡ በማድረግ የስልጠናውን ውጤት መገምገም፤

**ግብ 10፡- የትብብር መድረኩ የአባል ከተሞች ቁጥር ከፍ እንዲል ማድረግ**

ተግባር 1፡- በየክልሎች ከሚገኙ ከተሞች አባል መሆን የሚችሉትን በመለየት እና በማደራጀት እገዛ ማድረግ፤

ተግባር 2፡- በደብዳቤ፣ በስልክና በአካል በመንቀሳቀስ የተቀመጠውን ግብ ለማሳካት ከአባል ከተሞች የገቢ ማሰባሰቢያ ስራ መስራት፤

ተግባር 3፡- አባል ለሚሆኑ እና ክፍያቸውን ለሚያጠናቅቁ አባል ከተሞች የምስጋና ደብዳቤና ደረሰኝ መላክ፤

ተግባር 4፡- የአባልነት መስፈርቱን ማሟላት የቻሉትን ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው በማቅረብ ማጸደቅ፡፡

**ግብ 11፡- የትብብር መድረኩ የ"UCLGA" ሙሉ አባል እንዲሆን ማድረግ**

ተግባር 1፡- ከ"UCLGA" ጋር ትብብር መድረኩ አባል ስለሚሆንበት ሁኔታ በደብዳቤ ጥያቄ ማቅረብ ላይ መሳተፍ፤

ተግባር 2፡- አመታዊ የአባልነት ክፍያ መፈጸም፣

ተግባር 3፡- የአህጉር አቀፉ ትብብር ሙሉ አባል በመሆን ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፡፡

**ግብ 12፡- በከተሞች እህትማማችነት ጉድኝት ዙሪያ ወቅታዊ መልካም ተሞክሮዎች ላይ ያተኮረ በአባል ከተሞችና ባለድርሻ አካላት መካከል አንድ የልምድ ልውውጥ አውደ ጥናት ይካሄዳል፡፡**

ተግባር 1፡- ከዳሰሳ ጥናቱ በመነሳት ለበጀት አመቱ የልምድ ልውውጥ ፍላጎት መለየት፤

ተግባር 2፡- የአውደ ጥናቱን የስራ መዘክርና መርሀ ግብር ማዘጋጀት፤

ተግባር 3፡- ለአውደ ጥናቱ የሚሆኑ ተሞክሮዎችን ከከተሞች መሰብሰብ፤

ተግባር 4፡- ከከተሞች የተሰበሰቡ ተሞክሮዎችን በሳይንሳዊ የመቀመሪያ ዘዴ በመጠቀም ማሳተም፤

ተግባር 5፡- በአውደ ጥናቱ ላይ ተሳታፊ የሚሆኑ አካላትን መለየት፤

ተግባር 6፡- ለአውደ ጥናቱ የስብሰባ ቦታና ለተግባር ምልከታ የሚያመች ከተማ መለየት፤

ተግባር 7፡- በስብሰባው የሚገኙ ተሳታፊዎችን ጥሪ ማድረግና አውደ ጥናቱን ማካሄድ፤

ተግባር 8፡- የአውደ ጥናቱን አካሄድ መገምገምና ሪፖርት በማዘጋጀት ማሳተም፤

ተግባር 9፡- የታተሙ የአውደ ጥናት ሪፖርት ለተሳተፉና ላልተሳተፉ ከተሞች ማስተላለፍ፤

**ግብ 13፡- የከተሞች እህትማማችነት ጉድኝት ምስረታ እና ማጠናከሪያ ዙሪያ 1 የአሰራር ማንዋል ይዘጋጃል፡፡**

ተግባር 1፡- ዝክረተግባር ዝግጅት፤

ተግባር 2፡- በዝክረ-ተግባሩ መሠረት የሎጂስቲክስ ዝግጅት ማድረግ፤

ተግባር 3፡- መስፈርት በማዘጋጀት በአገር ውስጥ የሰነድ ማዘጋጃ ተቋምና ቦታ መምረጥ፤

ተግባር 4፡- የሰነድ ዝግጅት 1 የሥራ ቡድን (working group) ማቋቋም፤

ተግባር 5፡- 1 የአሰራር ማንዋል ዝግጅት፣

ተግባር 6፡- በሰነዱ ላይ ግብዓት ማሰባሰብ እና ማጻበር፡፡

## 2.1.2. የትብብር መድረኩን ዓላማና ተልዕኮ ለማሳካት የሚያስችሉ ግቦችና ተግባራት

**ፕሮጀክት አንድ፡ የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ አባል ከተማ አመራሮችና ባለሙያዎች የስልጠና እና የልምድ ልውውጥ ስራ ፕሮጀክት/ULGE: Uniting Local Governments in Ethiopia Project/**

**ግብ 1፡- በ "Servant Leadership, Critical thinking & problem solving, Organizational conflict management" የስልጠና ርዕሶች ዙሪያ ለ55 የአባል ከተሞች አመራሮችና ባለሙያዎች /30%ሴቶች/ የአቅም ግንባታ ስልጠና ይሰጣል፡፡**

ተግባር 1፡- ዝክረተግባር ዝግጅት፤

ተግባር 2፡- በዝክረ-ተግባሩ መሠረት የሎጂስቲክስ ዝግጅት ማድረግ፤

ተግባር 3፡- መስፈርት በማዘጋጀት በአገር ውስጥ የስልጠና ተቋምና ቦታ መምረጥ፤

ተግባር 4፡- ሰልጣኞችን መለየትና ጥሪ ማስተላለፍ፤

ተግባር 5፡- ለ55 አመራችና ባለሙያዎች ስልጠና ይሰጣል፤

ተግባር 6፡- የስልጠናውን አካሄድና ውጤት መገምገምና ሪፖርት ማዘጋጀት፤

**ግብ 2፡- በከተማ ፕላን ዝግጅትና ትግበራ፣ በከተሞች አየር ንብረት ተጽዕኖ መቋቋሚያ ዙሪያ ወቅታዊ መልካም ተሞክሮዎች ላይ ያተኮረ ለ80 አባል ከተሞችና ባለድርሻ አካላት መካከል አንድ የልምድ ልውውጥ አውደ ጥናት ይካሄዳል፡፡**

ተግባር 1፡- ከዳሰሳ ጥናቱ በመነሳት ለበጀት አመቱ የልምድ ልውውጥ ፍላጎት መለየት፤

ተግባር 2፡- የአውደ ጥናቱን የስራ መዘክርና መርሀ ግብር ማዘጋጀት፤

ተግባር 3፡- ለአውደ ጥናቱ የሚሆኑ ተሞክሮዎችን ከከተሞች መሰብሰብ፤

ተግባር 4፡- ከከተሞች የተሰበሰቡ ተሞክሮዎችን በሳይንሳዊ የመቀመሪያ ዘዴ በመጠቀም ማሳተም፤

ተግባር 5፡- በአውደ ጥናቱ ላይ ተሳታፊ የሚሆኑ አካላትን መለየት፤

ተግባር 6፡- ለአውደ ጥናቱ የስብሰባ ቦታና ለተግባር ምልከታ የሚያመች ከተማ መለየት፤

ተግባር 7፡- በስብሰባው የሚገኙ ተሳታፊዎችን ጥሪ ማድረግና አውደ ጥናቱን ማካሄድ፤

ተግባር 8፡- የአውደ ጥናቱን አካሄድ መገምገምና ሪፖርት በማዘጋጀት ማሳተም፤

ተግባር 9፡- የታተሙ የአውደ ጥናት ሪፖርት ለተሳተፉና ላልተሳተፉ ከተሞች ማስተላለፍ፤

**ግብ 3፡- በከተሞች መልካም አስተዳደር ዙሪያ ወቅታዊ መልካም ተሞክሮዎች ላይ ያተኮረ በአባል ከተሞችና ባለድርሻ አካላት መካከል አንድ የልምድ ልውውጥ አውደ ጥናት ይካሄዳል፡፡**

ተግባር 1፡- ከዳሰሳ ጥናቱ በመነሳት ለበጀት አመቱ የልምድ ልውውጥ ፍላጎት መለየት፤

ተግባር 2፡- የአውደ ጥናቱን የስራ መዘክርና መርሀ ግብር ማዘጋጀት፤

ተግባር 3፡- ለአውደ ጥናቱ የሚሆኑ ተሞክሮዎችን ከከተሞች መሰብሰብ፤

ተግባር 4፡- ከከተሞች የተሰበሰቡ ተሞክሮዎችን በሳይንሳዊ የመቀመሪያ ዘዴ በመጠቀም ማሳተም፤

ተግባር 5፡- በአውደ ጥናቱ ላይ ተሳታፊ የሚሆኑ አካላትን መለየት፤

ተግባር 6፡- ለአውደ ጥናቱ የስብሰባ ቦታና ለተግባር ምልከታ የሚያመች ከተማ መለየት፤

ተግባር 7፡- በስብሰባው የሚገኙ ተሳታፊዎችን ጥሪ ማድረግና አውደ ጥናቱን ማካሄድ፤

ተግባር 8፡- የአውደ ጥናቱን አካሄድ መገምገምና ሪፖርት በማዘጋጀት ማሳተም፤

ተግባር 9፡- የታተሙ የአውደ ጥናት ሪፖርት ለተሳተፉና ላልተሳተፉ ከተሞች ማስተላለፍ፤

**ግብ 4፡- ባልተማከለ አስተዳደር ዙሪያ ወቅታዊ መልካም ተሞክሮዎች ላይ ያተኮረ በአባል ከተሞችና ባለድርሻ አካላት መካከል አንድ የልምድ ልውውጥ አውደ ጥናት ይካሄዳል፡፡**

ተግባር 1፡- ከዳሰሳ ጥናቱ በመነሳት ለበጀት አመቱ የልምድ ልውውጥ ፍላጎት መለየት፤

ተግባር 2፡- የአውደ ጥናቱን የስራ መዘክርና መርሀ ግብር ማዘጋጀት፤

ተግባር 3፡- ለአውደ ጥናቱ የሚሆኑ ተሞክሮዎችን ከከተሞች መሰብሰብ፤

ተግባር 4፡- ከከተሞች የተሰበሰቡ ተሞክሮዎችን በሳይንሳዊ የመቀመሪያ ዘዴ በመጠቀም ማሳተም፤

ተግባር 5፡- በአውደ ጥናቱ ላይ ተሳታፊ የሚሆኑ አካላትን መለየት፤

ተግባር 6፡- ለአውደ ጥናቱ የስብሰባ ቦታና ለተግባር ምልከታ የሚያመች ከተማ መለየት፤

ተግባር 7፡- በስብሰባው የሚገኙ ተሳታፊዎችን ጥሪ ማድረግና አውደ ጥናቱን ማካሄድ፤

ተግባር 8፡- የአውደ ጥናቱን አካሄድ መገምገምና ሪፖርት በማዘጋጀት ማሳተም፤

ተግባር 9፡- የታተሙ የአውደ ጥናት ሪፖርት ለተሳተፉና ላልተሳተፉ ከተሞች ማስተላለፍ፡፡

**ግብ 5፡- በተለያዩ የውጭ ሀገራት በሚዘጋጁ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች ላይ አስር የአባል ከተማ ከንቲባዎች/ምክትል ከንቲባዎች/ማዘጋጃቤት ስራ አስኪያጆች ተሳታፊ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡**

ተግባር 1፡- ዝክረ ተግባር ማዘጋጀት፤

ተግባር 2፡- በወጪ መጋራት ዙሪያ ከከተሞች ጋር ምክክር ማድረግ፤

ተግባር 3፡- ለስልጠና ተሳታፊዎች የግብዣ ደብዳቤ ("invitation letter") እንዲመጣላቸው ማድረግ፤

ተግባር 4፡- ለስልጠና ተሳታፊዎች ቪዛ እንዲያገኙ ማመቻቸት፤

ተግባር 5፡- ለሰልጣኞች ተገቢውን ወጪና ክፍያ ማመቻቸት፤

ተግባር 6፡- ሰልጣኞች ከስልጠናው በኋላ ያገኙትን ውጤት በመቀመር ሪፖርት ማሳተም፤

ተግባር 7፡- የስልጠናውን ውጤት ሪፖርት ለአባል ከተሞች ማሰራጨት፡፡

**ግብ 6፡- የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ ስራአስፈጻሚ ቦርድ አመራሮች ኔዘርላንድ አገር ከሚገኘው ቪኤንጂ /VNG/ ጋር በአካል በመሄድ የልምድ ልውውጥ /Study tour and exposure visits/ እንዲያደርጉ ይደረጋል፡፡**

ተግባር 1፡- ዝክረተግባር ማዘጋጀት፤

ተግባር 2፡- ተሳታፊ የሚሆኑ አካላትን መለየት፤

ተግባር 3፡- ሎጅስቲክስ ማዘጋጀት፤

ተግባር 4፡- ለተሳታፊዎች ጥሪ ማድረግና ኦረንቴሽን መስጠት፤

ተግባር 5፡- ኔዘርላንድ በአካል በመሄድ የልምድ ልውውጥ **/Study tours and exposure visits/** ይደረጋል፤

ተግባር 6፡- የልምድ ልውጡን አካሄድ መገምገምና ሪፖርት በማዘጋጀት ማሳተም፤

ተግባር 7፡- የታተሙ የአውደ ጥናት ሪፖርት ለተሳተፉና ላልተሳተፉ ከተሞች ማስተላለፍ፡፡

**ፕሮጀክት ሁለት፡- The Netherlands-NUFFIC..... Orange Knowledge Program TMT+ ...........ፕሮጀክት**

**ግብ 1፡- የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን በማጠናቀቅ የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ /Inception mission and Training need assessment/ ይከናወናል፡፡**

ተግባር 1፡- ሰልጣኞችን መመልመል፤

ተግባር 2፡- የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ /TNA/ ማዘጋጀት፤

ተግባር 3፡- የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ የመጨረሻ ረቂቅ ሰነድ ላይ ከThe Hague Academy እና Local Experts ጋር ውይይት ይደረግበታል፤

ተግባር 4፡- ከ The Hague Academy ጋር በመሆን ኦንላይን የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ይከናወናል፤

ተግባር 5፡- The Hague Academy ለሚጠይቀው ቃለመጠይቅ መረጃ ይሰጣል፤

ተግባር 6፡- የውጤት ትንተና ይከናወናል፤

ተግባር 7፡- በ The Hague Academy ሪፖርት ይዘጋጃል፤

**ግብ 2፡- ለ15 ተሳታፊዎች አጠቃላይ የአሰልጣኞች ስልጠና /General training of trainers/ ይሰጣል፡፡**

ተግባር 1፡- በ The Hague Academy እና Local Experts በኦንላይን የአሰልጣኞች ስልጠና ይሰጣል፤

ተግባር 2፡- በ The Hague Academy በአካል የአሰልጣኞች ስልጠና ይሰጣል፤

ተግባር 3፡- በ The Hague Academy TOT Refresher ይሰጣል፤

ተግባር 4፡- በ The Hague Academy ሪፖርት ይዘጋጃል፤

**ግብ 3፡- በመልካም አስተዳደርና ሰላም ግንባታ (goodgovernance and peacebuilding) ለ15 ተሳታፊዎች ስልጠና ይሰጣል፡፡**

ተግባር 1፡- ዝክረተግባር ዝግጅት፤

ተግባር 2፡- በዝክረ-ተግባሩ መሠረት የሎጂስቲክስ ዝግጅት ማድረግ፤

ተግባር 3፡- መስፈርት በማዘጋጀት በአገር ውስጥ የስልጠና ተቋምና ቦታ መምረጥ፤

ተግባር 4፡- የተለዩ ሰልጣኞችን ጥሪ ማስተላለፍ፤

ተግባር 5፡- የስልጠና ሰነድ ይዘጋጃል፤

ተግባር 6፡- ስልጠናው እንዲካሄድ ማድረግ፤

ተግባር 7፡- የስልጠናውን አካሄድና ውጤት መገምገምና ሪፖርት ማዘጋጀት፤

**ግብ 4፡- በአካታች የከተማ ፕላን ዝግጅትና ትግበራ (Inclusive and Participatory Urban Planning) ለ15 ተሳታፊዎች ስልጠና ይሰጣል፡፡**

ተግባር 1፡- ዝክረተግባር ዝግጅት፤

ተግባር 2፡- በዝክረ-ተግባሩ መሠረት የሎጂስቲክስ ዝግጅት ማድረግ፤

ተግባር 3፡- መስፈርት በማዘጋጀት በአገር ውስጥ የስልጠና ተቋምና ቦታ መምረጥ፤

ተግባር 4፡- የተለዩ ሰልጣኞችን ጥሪ ማስተላለፍ፤

ተግባር 5፡- የስልጠና ሰነድ ይዘጋጃል፤

ተግባር 6፡- ስልጠናው እንዲካሄድ ማድረግ፤

ተግባር 7፡- የስልጠናውን አካሄድና ውጤት መገምገምና ሪፖርት ማዘጋጀት፤

**ግብ 5፡- በከተሞች መልካም አስተዳደርና በአካታች የከተማ ፕላን ዝግጅትና ትግበራ 2 የስልጠና ሞጁሎችና 2 ዝርዝር ማንዋሎች ይዘጋጃሉ፡፡**

ተግባር 1፡- ዝክረተግባር ማዘጋጀት፤

ተግባር 2፡- የስራ ቡድን ("working group") ማቋቋም፤

ተግባር 3፡- መረጃ መሰብሰቢያ ቼክ ሊስት ማዘጋጀት፤

ተግባር 4፡- መረጃ መሰብሰብና ማደራጀት፤

ተግባር 5፡- መረጃዎችን መተንተንና ረቂቅ ሞጁሎችና ማንዋሎች ማዘጋጀት፤

ተግባር 6፡- ሰነዶቹ ላይ ግብዓት ማሰባሰብና ሰነዱን ማዳበር፤

ተግባር 7፡- ሰነዶቹን የመጨረሻ ቅርጽ በማስያዝ ለዳይሬክተር ጀነራል ማቅረብ፤

ተግባር 8፡- ሰነዶቹን ማሳተም እና ለስልጠና ዝግጁ ማድረግ፡፡

**ግብ 6፡- በከተሞች መልካም አስተዳደር እና በሰላም ግንባታ /Good local governance & peacebuilding/ እንዲሁም በአካታች የከተማ ፕላን ዝግጅትና ትግበራ /Inclusive Urban Planning/ ዙሪያ በ2 ከተማ አስተዳደሮች በድምሩ ለ40 አመራሮችና ባለሙያዎች /30%ሴቶች/ በፓይለት ደረጃ የአቅም ግንባታ ስልጠና ይሰጣል፡፡**

ተግባር 1፡- ዝክረተግባር ዝግጅት፤

ተግባር 2፡- በዝክረ-ተግባሩ መሠረት የሎጂስቲክስ ዝግጅት ማድረግ፤

ተግባር 3፡- መስፈርት በማዘጋጀት በአገር ውስጥ የስልጠና ተቋምና ቦታ መምረጥ፤

ተግባር 4፡- ሰልጣኞችን መለየትና ጥሪ ማስተላለፍ፤

ተግባር 5፡- ስልጠናው እንዲካሄድ ማድረግ፤

ተግባር 6፡- የስልጠናውን አካሄድና ውጤት መገምገምና ሪፖርት ማዘጋጀት፤

**ግብ 7፡- ለትብብር መድረኩ ሰራተኞች በህብረተሰብ ተሳትፎና በአካታች አስተዳደር /Citizen Participation and Inclusive Governance/፣ በስርዓተ ጾታ ምላሽ ሰጪ አስተዳደር /Gender Responsive Governance/ እና ግጭት፣ የህግ የበላይነት እና የአካባቢ ደህንነት /Conflict, Rule of Law and Local Security/ አጫጭር የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡**

ተግባር 1፡- ዝክረተግባር ዝግጅት፤

ተግባር 2፡- በዝክረ-ተግባሩ መሠረት የሎጂስቲክስ ዝግጅት ማድረግ፤

ተግባር 3፡- ስልጠናው እንዲካሄድ ማድረግ፤

ተግባር 4፡- የስልጠናውን አካሄድና ውጤት መገምገምና ሪፖርት ማዘጋጀት፤

**ግብ 8፡- የማጠቃለያ ምዘና፣ ሰርቲፊኬት እና ክትትል ስራዎች ተከናውነው ለቀጣይ የፕሮግራም ዘላቂነትና ወደ ሌሎች አባል ከተሞች የሚሰፋበት ሁኔታ ይረጋገጣል፡፡**

ተግባር 1፡- ዝክረተግባር ዝግጅት፤

ተግባር 2፡- በዝክረ-ተግባሩ መሠረት የሎጂስቲክስ ዝግጅት ማድረግ፤

ተግባር 3፡- ተሳታፊዎችን መለየትና ጥሪ ማስተላለፍ፤

ተግባር 4፡- The Hague Academy, ECA እና Local Experts የሚሳተፉበት የማጠቃለያ አውደጥናት ይካሄዳል፤

ተግባር 5፡- በTHA የማጠቃለያ የምዘና ሪፖርት ማዘጋጀት፡፡

## ፕሮጀክት ሶስት፡- የ9ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ፕሮጀክት

**ግብ 1፡- ለ9ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም አዘጋጅ አሶሳ ከተማ አስተዳደር አንድ ጊዜ የቅድመ ዝግጅት ድጋፍ ይደረጋል፡፡**

ተግባር 1፡- ለክትትልና ድጋፍ ዝክረ-ተግባር ማዘጋጀት፤

ተግባር 2፡- ለክትትልና ድጋፍ ቼክ ሊስት ማዘጋጀት፤

ተግባር 3፡- ለክትትልና ድጋፍ የሎጂስቲክ ዝግጅት ማድረግና የሰው ኃይል ማሰማራት፤

ተግባር 4፡- በከተማው በመገኘት ክትትልና ድጋፍ ማካሄድ፤

ተግባር 5፡- ለከተማ አስተዳደሩ በግንባር/በአካል ግብረ-መልስ መስጠት፤

ተግባር 6፡- ለከተሞቹ በጽሑፍ ግብረ-መልስ መስጠት፤

ተግባር 7፡- ክትትልና ድጋፉን አስመልክቶ ሪፖርት ማቅረብ፤

**ግብ 2፡- የ9ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም በአሶሳ ከተማ አስተዳደር በደማቅ ሁኔታ እንዲካሄድ ተሳታፊ ከተሞች እንዲመዘገቡና በአጥጋቢ ሁኔታ እንዲሳተፉ ይደረጋል፡፡**

ተግባር 1፡- ተሳታፊ ከተሞችን መለየት፤

ተግባር 2፡- የምዝገባ ቅጻቅቆች ማዘጋጀት፤

ተግባር 3፡- ምዝገባ ማከናወን፤

ተግባር 4፡- ምዝገባውን አስመልክቶ ሪፖርት ማዘጋጀት፤

ተግባር 5፡- የምዝገባውን ሪፖርት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በወቅቱ ሪፖርት ማድረግ፤

**ግብ 3፡- የ9ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም በአሶሳ ከተማ አስተዳደር በደማቅ ሁኔታ እንዲካሄድ አባል ከተሞች ተሳትፎና አጠቃላይ አፈጻጸም ሪፖርት በማዘጋጀት ከሚ/ር መ/ቤቱ ጋር የመገምገም ስራ ይከናወናል፡፡**

ተግባር 1፡- ዝክረተግባር ማዘጋጀት፤

ተግባር 2፡- የከተሞች የተሳትፎ ደረጃን መለየት፤

ተግባር 3፡- የአፈጻጸምና የግምገማ ሰነድ ማዘጋጀት፤

ተግባር 4፡- ሪፖርቱን ለተሳታፊ አካላት ማሰራጨት፡፡

**ፕሮጀክት አራት፡-**Japan Embassy-ECA Joint Public Park Development Project

**ግብ 1፡- ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የልደታ ክፍለከተማ የህዝብ ፓርክ ልማት ከከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ፈንድ የማፈላለግ ስራ ይከናወናል፡፡**

ተግባር 1፡- ፕሮጀክት ፕሮፖዛል ማዘጋጀት፤

ተግባር 2፡- ፕሮጀክት ፈንድ ማፈላለግ፤

ተግባር 3፡- ከሚኒስቴር መስርያቤቱ እና ከዶነሩ ጋር የስምምነት ሰነድ /Memorandum of Understanding/ መፈራረም፤

ተግባር 4፡-ለፕሮጀክቱ የባንክ አካውንት ለመክፈት የትብብር መድረኩን ስራ አስፈጻሚ ቦርድ በቃለጉባዔ ማስወሰን፤

ተግባር 5፡- የባንክ አካውንት መክፈት፤

ተግባር 6፡- ገንዘቡ ገቢ መደረጉን ክትትል ማድረግ፡፡

**ግብ 2፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የልደታ ክፍለከተማ የህዝብ ፓርክ ልማት በፕሮጀክት ፕሮፖዛሉ መሰረት መልማቱን ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል፡፡**

ተግባር 1፡- የክትትልና ድጋፍ ዝክረተግባር ይዘጋጃል፤

ተግባር 2፡- ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ የፕሮጅክት ማስፈጸሚያ ግዢ ይከናወናል፤

ተግባር 3፡- የተገዙ ቁሳቁሶች ለሚኒስቴር መ/ቤቱ አሰራሩ ተጠብቆ እንዲተላለፍ ይደረጋል፤

ተግባር 4፡- የፕሮጀክት ትግበራ እና ኦዲት ሪፖርት ይዘጋጃል፡፡

## 2.4. እቅዱን በመተግበር ሂደት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ታሳቢ ስጋቶችና የመፍትሄ እርምጃዎች

### 2.4.1. ታሳቢ ስጋቶች

- የሰራተኛ ፍልሰት፤
- ከአባል ከተሞችና ከለጋሽ ድርጅቶች የሚሰበሰብ ገቢ ወቅቱን ጠብቆ ያለመገኘት፤
- የአባል ከተሞች አመራሮች ለተሞክሮ ቅመራው ትኩረት ያለመስጠት፤
- የቢሮ ምቹ ያለመሆን መቀጠል፤
- ከተለያዩ አካላት ጋር በቅንጅት የሚፈጸሙ ስራዎች በተያዘላቸው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት አለመከናወን፤
- በትብብር መድረኩ በሚዘጋጁ ስልጠናዎችና አውደ ጥናቶች በበቂ ሁኔታ ያለመሳተፍ፤

### 2.4.2. ታሳቢ የመፍትሄ እርምጃዎች

- የሰራተኞች የደሞዝና ጥቅማ ጥቅሞች ማሻሻል፤
- የቅንጅት ስራዎችን በመለየትና ለባለ ድርሻ አካላት በማሳወቅ የጋራ ትስስር ፈጥሮ ለውጤታማነት መንቀሳቀስ፤
- ከአባል ከተሞችና ከለጋሽ ድርጅቶች የሚሰበሰብ ገቢ ወቅቱን ጠብቆ እንዲመጣ በዋነኝነት ጠንክሮ መስራት፤
- የአባል ከተሞች አመራሮች ለተሞክሮ ቅመራው ትኩረት እንዲሰጡት ተገቢውን ክትትል ማድረግ፤
- የቢሮ ችግርን በዘላቂነት ለመፍታት ከፌደራል ቤቶች ኮርፖሬሽን በተመጣጣኝ ዋጋ ለማግኘት መስራት እና በስራ አስፈጻሚ ደረጃ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጋር በሊዝ ምደባ መሬት የሚገኝበት ሁኔታ ላይ ጥያቄ ማቅረብ፤
- በትብብር መድረኩ በሚዘጋጁ ስልጠናዎችና አውደ ጥናቶች በበቂ ሁኔታ መሳተፍ እንዲችሉ አባል ከተሞችን ማነቃቃትና መቀስቀስ፡፡

## ክፍል ሦስት፡- የክትትል፣ ግምገማና ግብረ መልስ ሥርዓት

በትብብር መድረኩ የታቀዱ ስራዎች በተፈለገውና በታቀደው ጊዜ ለማከናወን እንዲያስችል በየዳይሬክቶሬቱ የታቀዱ ስራዎች መከናወናቸውን ለመከታተል የሚያስችሉ የክትትልና የሪፖርት ስራዎችን የሚሰሩ ሲሆን በተቀመጠው የክትትልና ግምገማ ስርዓት ጥናት መሰረት ተግባራዊ ይሆናል፡፡

- የአሰራር መመሪያ ሰነዶች ዝርዝር አፈጻጸም ወጥ የሆኑ ፎርምቶችን /ቼክሊስቶች/ በመጠቀም ተግባራዊ ማድረግ፤
- የሩብ ዓመት፣ የግማሽ ዓመትና ዓመታዊ ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶችን በማዘጋጀትና በዳይሬክቶሬት ደረጃ ክትትልና ግምገማ ማድረግ፤
- በእቅድ የተያዙ ስራዎችን አፈጻጸምና ያጋጠሙ ችግሮችን በየሩብ ዓመቱ በድርጅቱ አስተዳደር አባላት ጋር በጋራ መገምገም ወቅታዊ የማሻሻያ እርምጃዎችን መውሰድ፡፡

## ማጠቃለያ

ይህ ዕቅድ ከወቅቱ ትኩረት አኳያ አዳዲስ ሥራዎችን ለመስራት የተዘጋጀ ሲሆን ዕቅዱን ለማሳካትና አጠቃላይ የትብብር መድረኩን አፈጻጸም ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ ይጠበቃል፡፡ በቀጣዩ ዓመት ከዚህ ልምድ በመነሳት የተሻለ ስራ መስራት ይቻል ዘንድ የዚህ እቅድ አፈጻጸም መሰረት በመሆኑ አቅምን አሟጦ መስራትን ይጠይቃል፡፡ በአፈጻጸም ላይ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣ መሻሻል የሚያስፈልጋቸውን ጉዳዮች በጥናት በመለየት በቀጣይ እንዲሻሻሉ በማድረግ ላይ ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣል፡፡ ይህ ዕቅድ በውስጡ የተመለከቱትን ዓላማና ግቦች ለማሳካት የሚያስችሉ ሥራዎችን ይዟል፡፡ ለአፈጻጸሙ የሚከተለው መርሆም የትብብር መድረኩ ባለሙያዎች ሥራቸውን በተናጥል ሳይሆን ቅንጅታዊና የቡድን የአሠራር ዘዴን በመከተል በየጊዜው የላቀ ውጤትን ማስመዝገብ በሚያስችል መንገድ እንዲያከናውኑ ታሳቢ ያደርጋል፡፡ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴውም ቅርብ ድጋፍና ክትትል ለእቅዱ መሳካት ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል፡፡